ቅጽ 1 ቁጥር 27 ታህሳስ 2003

# የ2003 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ተገመገመ

በኤጀንሲው ሕዳር 29 ቀን 2003 ዓ.ም በተደረገ አጠቃላይ የሠራተኞች ስብሰባ በ2003 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ግምገማ ተካሄደ፡፡

ግምገማው መሠረት ያደረገው በ2003 በጀት ዓመት ለመጀመሪያው ሩብ ዓመት ከታቀዱት ተግባራት መካከል የማስፈፀም አቅምን በማጎልበት ረገድ የሪፎርሙን 5 ንዑሳን ፕሮግራሞች በመተግበር አሠራርን ማሻሻልና መልካም የሥራ አካባቢ ሥነ-ምግባርን ከማስፈን፣ የሰው ሀብት ልማትን ውጤታማ እንዲሆን ከማስቻል፣ የግዢ ፋይናንስ ንብረት አስተዳደርና አገልግሎት ከአቀርቦት አኳያ፣ የግዢ ፋይናንስ ንብረት አስተዳደርና የዕቅድ አፈጻጸም ፕሮግራሞችን ኦዲት ከማድረግ፣ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን የማስፋፋትና የመረጃ ስርዓት ዝርጋታ አፈጻጸምን ክትትልና ግምገማ በማካሄድ የኤጀንሲውን ዓላማ በፕሮግራም እንዲሠራ ከማስቻል፣ ሕግ ነክ ጉዳዮችን በመከታተልና በማስፈፀም እልባት እንዲያገኙ ከማድረግ አኳያ ሲሆን፣ በዓላማ አስፈጻሚው የተከናወኑ ተግባራትን አስመልክቶ የአሠራር ክፍተቶችን በመፈተሽና የደንበኞችን ፍላጎት በጥናት በመለየት የአገልግሎት አሰጣጥ እንዲሻሻል ከማድረግ አኳያ፣ የመረጃ ሀብቶችን አሰባሰቦ፣ አደራጅቶ፣ እንክብካቤና ጥበቃ አድርጎ ለአገልግሎት ከማብቃት፣ ውጤታማ የሰው ኃይል ልማትና አጠቃቀምን በማስፈን በቴክኖሎጂ የታገዘ ቀልጣፋ አገልግሎት ከመስጠት፣ በመረጃ ሀብቶች በመጠቀም የንባብና የምርምር ባህሉ የዳበረ ህብረተሰብ

ለመፍጠር ዓላማ ተኮር የማስተዋወቅ ኘሮግራሞችን ከማካሄድና የስርዓተጾታንና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጉዳዮችን ሜይንስትሪም በማድረግና በዕቅድ አካቶ በመተግበር በጉዳዮቹ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን ከመቀነስ አኳያ የተከናወኑ ስራዎች ላይ ትኩረት አድርጎ የተካሄደ ግምገማ ነው፡፡

በግምገማው ሠራተኞች በርካታ ጥያቄዎችና አስተያየቶችን አንስተው ውይይት የተካሄደባቸው ሲሆን ውይይቱን ተከትሎ ለተነሱ ጥያቄዎች በሚመለከታቸው የስራ ክፍሎችና ከመድረክ ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

በግምገማው በሩብዓመቱ የስራ አመራሩ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በየወሩ መገምገም መቻሉና በየሩብ ዓመቱ በሠራተኞቹ እንዲገመገም መደረጉ በጠንካራ ጎኑ የሚጠቀስ መሆኑ በሪፖርቱ የተገለፀ ሲሆን፣ በሩብ ዓመቱ ያልተከናወኑ ተግባራት በሁለተኛው ሩብ ዓመት ዕቅድ ውስጥ ተካተው እንዲተገበሩ

ማድረግና በዚሁ ሩብ ዓመት የዕቅድ ክንውን ውጤትን በማጠናከርና የተገኙትን ጠንካራ ጎኖች ተሞክሮ በመውሰድ በዕቅዱ ላይ የተቀመጡትን የሚጠበቁ ውጤቶች ለማስመዝገብ ከአንደኛው ሩብ ዓመት የበለጠ ለታቀዱ ተግባራት ትኩረት ሰጥቶ በቅንጅት በመስራት በቀጣዮቹ ሩብ ዓመታት ከዚህ የበለጠ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚቻል በመግለጽ ግምገማውን ማጠቃለል ተችሏል፡፡

## ሲምፖዚየም ተካሄደ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ የጽሁፍ ቅርሶች አስመዝጋቢ ኮሚቴ (Memory of the World) ጋር በመተባበር "የአገሪቱን የጽሁፍ ቅርሶች መጠበቅና መንከባከብ" በሚል መሪ ቃል ለሁለት ቀናት የቆየ ሲምፖዚየም አካሄደ፡፡

ሲምፖዚየሙ ሕዳር 14 እና 15 ቀን 2003 ዓ.ም በቸርችል ሆቴል የተካሄደ ሲሆን፣ መሠረታዊ ዓላማው የጽሁፍ ቅርሶች ከግለሰባዊ የታሪክ ፋይዳነት አልፈው የሀገር ብሎም የዓለም ታሪክ መዘክር በመሆናቸው ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባል በሚል የተዘጋጀ ሲሆን፣ ለተግባራዊነቱ ኃላፊነቱን ለመንግስት ብቻ የምንተወው ሳይሆን እንደዜጋ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚመለከተውና በቀዳሚነትም መሠለፍና ኃላፊነትን መውሰድ እንዳለበት ተገቢውን ግንዛቤ ማስጨበጥ ላይ መሠረት አድርጎ የተካሄደ ነበር፡፡

ሲምፖዚየሙን በንግግር የከፈቱት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሚ/ር ዴኤታ ክቡር አቶ ዳውድ መሀመድ ሲሆኑ፣ እሳቸውን ተከትሎ በኢትዮጵያ የዩኔስኮ ተወካይ ዶ/ር አሌክሳንድሮስ ማካሪጋኪስ እንዲሁም በኢትዮጵያ ብሔራዊ የጽሁፍ ቅርሶች አስመዝጋቢ ኮሚቴ በኩል ሊቀመንበሩ አቶ እሸቱ ዮሐንስ በተከታታይ ንግግር አድርገዋል፡፡

በሲምፖዚየሙ ከጽሁፍ ቅርሶች አጠባበቅና አያያዝ ብሎም ኃላፊነት ጋር ተያይዞ በመጀመሪያው ቀን በመጀመሪያው ሴሽን "The Status of Islamic Documentary Heritage in Ethiopia" በሁለተኛው ሴሽን ደግሞ "The Manuscript Tradition of Ethiopian Orthodox Tewahdo Church" በሚሉ ርዕሶች ዙሪያ ሁለት ጥናታዊ ጽሁፎች ቀርበው ሠፊ ውይይት የተካሄደባቸው ሲሆን፣ በተመሳሳይ በሁለተኛው ቀንም "Endangered Species; the State of Manuscript Heritage in Ethiopia" በሚል እንዲሁ አንድ ጥናታዊ ፅሁፍ ቀርቦ ውይይት ተካሂዶበታል፡፡

በሁለቱ ቀናት ቆይታ የተካሄደው ውይይት በተሳታፊዎች ዘንድ ትልቅ ግብአትን /አቅምን ከመፍጠሩም ባሻገር በውይይቱ ወቅት ይነሱ በነበሩ ጥያቄዎችና አስተያየቶች በዘርፉ መሠረታዊ ዕውቀቶችን መጨበጥ እንደተቻለ ከነበረው ተሳትፎ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በሲምፖዚየሙ ከ90 በላይ የሚሆኑ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅት ተወካዮች፣ ከክልልና ከማዕከል የተውጣጡ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

በሲምፖዚየሙ ማጠቃለያ ለቅርሶች ጥበቃና እንክብካቤ ሁሉም አካላት እንደዜጋ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በመግለጽ፣ በሁለቱ ቀናት የሲምፖዚየም ቆይታ ላይ ውይይት ከተደረገ በኂላ የጋራ የአቋም መግለጫ በማውጣት ኘሮግራሙን በተሳካ ሁኔታ ማጠቃለል ተችሏል፡፡

## በኤጀንሲው በሠራተኞች መካከል የሩጫ ውድድር ተካሄደ

ህዳር 23 ቀን 2003 ዓ.ም በየዓመቱ ህዳር 22 ቀን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚከበረውን የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ቀን ምክንያት በማድረግ እንደሀገር "ሁሉን አቀፍ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አገልግሎቶች ተደራሽነትና ሰብዓዊ መብቶች ለሁሉም" በሚል እንደ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ ደግሞ "ግልጽነትን በማስፈን የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ተጋላጭነትን እንቀንስ" በሚል መሪ ቃል በሠራተኞች መካከል የ2 ኪ.ሜትር የሩጫ ውድድር ተደረገ፡፡

ውድድሩ በኤጀንሲው ቅጥር ግቢ የተካሄደ ሲሆን፣ ዋና ዓላማው እንደ ሀገር ሁሉን አቀፍ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አገልግሎቶችን የመለየትና ከተደራሽነት አኳያ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችን አስመልክቶ ተገቢውን ግንዛቤ ለሠራተኞች ማስጨበጥ ሲሆን፣ እንደተቋምም ቀደም ሲል በዘርፉ እየተሠሩ ያሉ እንቅስቃሴዎችን ቀጣይ በማድረግ ረገድ ግልጽነት ከምንም በላይ ወሳኝ መሆኑንና የተጀመሩ የአቻ ለአቻ ውይይቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ከወዲሁ መሠረት ለመጣል ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡

በውድድሩ በርካታ ሠራተኞች የተሳተፉበት ሲሆን፣ ሁሉም ሠራተኞች ከውድድሩ አስቀድሞ እንደሀገር ለዓመቱ መሪ ቃል፣ እንደተቋም ደግሞ ለተቋሙ መሪ ቃል ተገዢ በመሆን እንሮጣለን ሲሉ መልዕክታቸውን በጋራ በማስተላለፍ በውድድሩ ተሳትፈዋል፡፡

ፕሮግራሙን በ1ኛ ደረጃ ዲኬቲ ኢትዮጵያ ቲሸርትና ኮፍያ በመስጠት በ2ኛ ደረጃ የስ ውሃ ድርጅት ከተወዳጅ ምርቶቹ ስፖንሰር ያደረጉት ሲሆን፣ የኤጀንሲው የፀረ.ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዴስክም ለተወዳዳሪዎች የማበረታቻ ሽልማትና የሻይ ቡና መስተንግዶውን በመሸፈን በ3ኛ ደረጃ ስፖንሰር በማድረግ ለፕሮግራሙ ስኬት ቁልፍ ሚና ተጫውቷል፡፡

በፕሮግራሙ ማጠቃለያ ከ1ኛ-3ኛ ለወጡ ለሁለቱም ጾታ ተወዳዳሪዎች ሽልማት የተሰጠ ሲሆን ፣ የሽልማት ሥነ-ሥርዓቱን ተከትሎ ለፕሮግራሙ መሳካት ጥረት ያደረጉ አካላትንና የውድድሩ ተሳታፊዎችን በማመስገን ፕሮግራሙን በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡

## በኤጀንሲው የማህበራዊ ጤና መድህን ስርዓትን ለማስፈፀም በወጣው ደንብ ላይ ውይይት ተደረገ

ሕዳር 27 ቀን 2003 ዓ.ም ለግማሽ ቀን በኤጀንሲው የመሰብሰቢያ አዳራሽ በተካሄደ ጠቅላላ የሠራተኞች ስብሰባ የማህበራዊ ጤና መድህን ስርዓትን ለማስፈፀም በወጣው የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ላይ ውይይት ተደረገ፡፡

የውይይቱ መሠረታዊ ዓላማ የማህበራዊ ጤና መድህን ስርዓትን ለማስፈፀም የወጣው ደንብ ተቀዳሚ ዓላማ /ተግባር/ ተጠቃሚው ህብረተሰብ /ሠራተኛ/ በጤና ተቋማት አገልግሎት በሚሻበት ወቅት አብዛኛውን ከኪስ የሚከፈል ወጪ በመቀነስ፣ ጥራት ያለውና ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት ሽፋን ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲያገኝ ማስቻል በመሆኑ ይህንኑ ተፈፃሚ ለማድረግ በቀረበው የጤና ኢንሹራንስ አዋጅ ዙሪያና በመተዳደሪያ ደንቡ ማንዋል ላይ ከሠራተኞቹ ጋር አስፈላጊውን ውይይት በማድረግ ደንቡን ሊያጎለብቱ የሚችሉ አስተያየቶችንና ማዳበሪያ የሚሆኑ ግብአትን ለማሠባሰብ ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡

በፕሮግራሙ መክፈቻ ለውይይት እንደመነሻ ያገለግላሉ በሚል ስለማህበራዊ የጤና መድህን ምንነት፣ ስርዓትና የመቋቋም አስፈላጊነት፣ ስለማህበራዊ ጤና መድህን ስርዓት ታሪካዊ አመጣጥ፣ ልዩ ባህርያትና ጥቅሞች፣ እንዲሁም በማህበራዊ የጤና መድህን ስርዓቱ የማይካተቱ ህክምናዎችን አስመልክቶ ሠፊ ገለፃ ተደርጓል፡፡

የቀረበውን ገለፃ ተከትሎ በሠራተኞች በርካታ ተያያዥና መሠረታዊ ጥያቄዎች ተነስተው ለአብዛኛዎቹ ከመድረክ ምላሽ የተሰጠባቸው ሲሆን፣ የተወሰኑት ሠፊ ማብራሪያን የሚሹና እንደግብዓት የሚወሰዱ በመሆናቸው እንዳለ ወደሚመለከተው አካል የሚተላለፍ /የሚደርሱ/ መሆናቸው ተገልጾ ውይይቱ ተጠቃሏል፡፡

## በደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ስልጠና ተሰጠ

በኤጀንሲው ከሕዳር 28-29 ቀን 2003 ዓ.ም ባሉት ሁለት ተከታታይ ቀናት ከተለያዩ የስራ ክፍሎች ለተውጣጡ 36 የኤጀንሲው ሠራተኞችና ባለሙያዎች በደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ስልጠና ተሰጠ፡፡

ስልጠናው በኤጀንሲው የሰው ሀብትና ልማት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት አማካኝነት የተዘጋጀ ሲሆን መሠረታዊ ዓላማው ደንበኞችን እንደየፍላጎታቸው ለማስተናገድ የሚያስችል መሠረታዊ የደንበኞች አያያዝና ስርዓት ላይ በማተኮር የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት አንዱና ዋነኛው ሲሆን ከዚሁ ጋር አገልግሎቱን በተሻለ መልኩ ለማስቀጠል ብሎም ቀልጣፋ ለማድረግ ደንበኞችን መለየት ቀዳሚው

ሲሆን፣ በተያያዘ ደንበኞች ፍላጎታቸው ምንድነው? በምን መልኩ መስተናገድ ይፈልጋሉ? የሚሉትን እንደዋና መነሻ በማድረግ ግንዛቤውን በስፋት መፍጠር ላይ ትኩረት አድርጎ የተሰጠ ነው፡፡

ከስልጠናው በኋላ ሰልጣኞች በስልጠና ቆይታቸው የስልጠናውን ጥሩ ጎን ከገለፁ በኋላ እንደተቋም በአገልግሎት አሰጣጥ ረገድ እንደዋና ችግር የተመለከቱትን ጠቁመው መፍትሔ ያሉትንም ሀሳብ አመላክተዋል፡፡

እንደ አጠቃላይ በቀጣይ በኤጀንሲው የተሻለ አገልግሎትና የተቀላጠፈ አሠራር ለማስፈን በተነሳሽነት በጋራ መስራት እንዳለባቸው አቋም የያዙበት ጥሩ የስልጠና ጊዜ እንደነበርም ከስልጠናው በኋላ ከተሰጡ አንዳንድ አስተያየቶች ለመረዳት ተችሏል፡፡

## ስልጠና ተሰጠ

በኤጀንሲው በቤተመጻሕፍት ሙያ ከህዳር 13 ቀን እስከ ታህሳስ 8 ቀን 2003 ዓ.ም ድረስ ባሉት ተከታታይ ቀናት በበጀት ዓመቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ከክልልና ከማዕከል ለተውጣጡ 28 የቤተመጻሕፍት ሠራተኞች በቤተመጻሕፍት አደረጃጀትና አገልግሎት አሰጣጥ ፣ በክላስፊኬሽን፣ በካታሎጊንግ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ ሙያዊ ስልጠና ተሰጠ፡፡

ስልጠናው በአምስት መርሃ ግብሮች ተከፍሎ በኤጀንሲው ባለሙያዎች የተሰጠ ሲሆን ዓላማው በየዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎችን የሙያ ክህሎታቸውን ማሳደግና በሙያቸው ማብቃት ላይ አተኩሮ የተሰጠ ነው፡፡

በስልጠናው ማጠናቀቂያ የስልጠናውን መጠናቀቅ ተከትሎ በተዘጋጀው የምረቃ ሥነ-ሥርዓት ላይ ሰልጣኞች የስልጠና ቆይታቸውንና በስልጠና ያገኙትን ሲገልፁ፣ ስልጠናው ባለሙያውን በተሰማራበት የሙያ መስክ ከማብቃት ባለፈ በዘርፉ ሠፊና መሠረታዊ ዕውቀትን ማስጨበጥ ያስቻለ ፕሮግራም ነው ብለውታል፤ አያይዘውም ባለሙያው ሙያውን እንደሙያ በፍቅር እንዲሠራበትና እንዲዘልቅበት በማድረግ ረገድም ትልቅ እገዛ የሚፈጥር ነው ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፤ እንደዋና ጉዳይ መታለፍ የማይገባው በማለት የሰጡት አስተያየት ስልጠናው ባለሙያውን በሙያው ማብቃት እስከሆነ ድረስ የስልጠና ጊዜው ያጠረ በመሆኑ ቢራዘም፣ የ  ስልጠና ቦታውም የቢሮ ፀጥታን ከማወክ አኳያ ከቢሮ አካባቢ ራቅ ብሎ የሚሰጥበት ሁኔታ ለወደፊቱ ቢመቻች የተሻለ እንደሚሆን ገልፀዋል፡፡

በመጨረሻም የሥነ-ሥርዓቱን መጠቃለል ተከትሎ ለሠልጣኞች የተዘጋጀላቸውን የተሳትፎ የምስክር ወረቀት በመስጠት ፕሮግራሙን በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ ከታህሳስ 11-22 ቀን 2003 ዓ.ም  ከማዕከልና ከክልል ለተውጣጡ 36 ሠልጣኞች በበጀት ዓመቱ ለሁለተኛ ጊዜ በሪከርድ ሥራ አመራር፣ በመዛግብት አስተዳደር ሙያ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ ሙያዊ  ስልጠና ተሰጥቷል፤ በተያያዘ የሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ከታህሳስ 13-15 ቀን

2003 ዓ.ም ድረስ በአዳማ ከተማ አዳማ ራስ ሆቴል ባዘጋጀው የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም ላይ ኤጀንሲው ተሳታፊ በመሆን በቤተመጻሕፍት ሙያ ከተለያዩ ወጣት ማህበራትና ከተለያዩ ክልሎች ለተውጣጡ ተሳታፊዎች የአንድ ቀን ስልጠና በኤጀንሲው ባለሙያዎች መሰጠቱ ታውቋል፡፡

## በመሰረታዊ የአሰራር ሂደት ለውጥ (BPR) ጥናት የሙከራ ትግበራ የአፈጻጸም ደረጃ ላይ ውይይት ተካሄደ

ህዳር 10 ቀን 2003ዓ.ም ለሙሉ ቀን በኤጀንሲው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ከባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተዘጋጅተው በቀረቡ 23 የ (BPR) የሙከራ ትግበራ የአፈጻጸም የትኩረት ነጥቦች ላይ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻህፍት ኤጀንሲ ሰራተኞች ውይይት አካሄዱ፡፡ ውይይቱን የመሩት የኤጀንሲው የለውጥ ትግበራ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት ጊ/ዳይሬክተር አቶ እሸቱ ዮሀንስና የመረጃ ሀብቶች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ጊ/ዳይሬክተር አቶ አህመድ አደም ናቸው፡፡

የውይይቱ መሰረታዊ ዓላማ በ (BPR) የሙከራ ትግበራ ወቅት፡- ከቅንጅታዊ አሰራር፣ ከተደራሽ ግቦች አንጻር፣ ከደንበኞች አስተያየት ከማሰባሰብ፣ ባለሙያዎችንና ሰራተኞችን ከማብቃት፣ የአሰራር ክፍተቶችን ከመገምገም፣ ከስራ ሂደቱ አንጻር ተናቦ ከመስራት፣ በሙከራ ወቅት የስራ ሂደቶች የሚያጋጥማቸውን ችግሮች በመመርመር የማሻሻያ ሃሳብ ከማቅረብና በሌሎችም ተዛማጅ የትኩረት ነጥቦች ላይ የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመፈተሽ ወደ ሙሉ ትግበራ የሚገባበትን ሁኔታ ከወዲሁ ለማመቻቸት ነው፡፡

በውይይቱ ወቅት በ (BPR) የሙከራ ትግበራ ወቅት የኤጀንሲው ጠንካራና ደካማ ጎኖች ናቸው ተብለው ከሰራተኞችና ከመድረክ በቀረቡ ነጥቦች ላይ ሰፊ ውይይት ተካሂዶባቸዋል፡፡

በጠንካራ ጎንነት እንደ አብነት ከተጠቀሱት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በማስፋፋት የመረጃ ስርአት ዝርጋታ መጀመሩ፣ የህጻናት ቤተ መጻህፍት መከፈቱ፣ የመረጃ ሀብቶችን ወደ ኤሌክትሮኒክስ ላይብረሪ ማኔጅመንት ሶፍት ዌር የመጫን ስራ መጀመሩና የድምጽ ላብራሪ (SOUND ARCHIVE) ለማቋቋም በጥረት ላይ መገኘቱ የሚሉት ተጠቃሽ ሲሆኑ፣ በደካማ ጎንነት ከተዘረዘሩት ደግሞ የ (BPR) ጥናቱ ቤተ መዛግብቱንና ቤተ መጻህፍቱን በአንድ የስራ ሂደት ቀላቅሏል፤ የሙከራ ትግበራው አሁንም ከ(functional) አሰራር የተላቀቀ አይደለም፤ ጥናቱ የአፈጻጸም ችግሮች አሉበት የሚሉና የመሳሰሉ አስተያይቶች ተሰንዝረዋል፡፡

በውይይቱ ማጠቃለያ ላይ በ (BPR) የሙከራ ትግበራ ወቅት በአፈጻጸም ሂደት ላጋጠሙ አሉታዊ የአፈጻጸም ደረጃዎች የተሻለ የአሰራር አቅጣጫን በመከተልና በአሰራር ለታዩ ክፍተቶች መፍትሄ በመስጠት ወደ ሙሉ ትግበራ የሚገባበትን መንገድ በመፈለግ ለኤጀንሲው እድገት ጠንክሮ መስራት ከሁሉም የኤጀንሲው ሰራተኞች የሚጠበቅ እንደሆነ ከውይይቱ ሰብሳቢ በውይይቱ ማጠቃለያ ተጠቁሟል፡፡